# በሥዕል የተደገፈ የዕባዳዎች አፈጻጸም ፍቅህ

## የእስላም ዝርዝር ሕግጋት ትምህርት በቀላል አቀራረብ

ጦሃራ | ሶላት | ጾም | ዘካ | ሐጅ



ዶክተር ዐብዱላህ ባህማም

ተርጓሚ

ሙሐመድ ጀማል ሙኽታር

## የተጠው’ዉዕ ሶላት

15

# የተጠው’ዉዕ ሶላት



**የተጠው’ዉዕ ሶላት**

ግዴታ ያልሆነና መስገዱ የተደነገገ ሶላት ነው፡፡

## የተጠው’ዉዕ ሶላት ትሩፋት

1. የተጠው’ዉዕ ሶላት አላህ ﷻ አገልጋይ ባሪያውን እንዲወደው ምክንያት ይሆናል፡፡ በሐዲስ አልቁድሲ እንደተመለከተው አላህ ﷻ እንዲህ ይላል፡- ‹‹ባሪያዬ እስክወደው ድረስ በነዋፍል (ግዴታ ያልሆኑ ተጨማሪ ዕባዳዎች በማከናወን) ወደኔ መቅረቡን ይቀጥላል፤ከወደድኩት ደግሞ የሚያይበት ማያው፣የሚሰማበት መስሚያው፣የሚሰነዝርበት እጅ እና የሚጓዝበት እግር እሆንለታለሁ፡፡ ከለመነኝ በእርግጥ እሰጠዋለሁ፤ከኔ መጠጊያና መጠበቂያ ከፈለገም በእርግጥ እጠብቀዋለሁ፡፡››[1]

2. የተጠው’ዉዕ ሶላት በግዴታ ሶላቶች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉድለቶችን ያካክሳል፡፡ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹በትንሣኤ ቀን ከሥራዎቻቸው ውስጥ ሰዎች በመጀመሪያ የሚጠየቁበት ሶላት ነው፡፡ ጌታችን እርሱ የበለጠውን የሚያውቅ እየሆነ ለመላእኮች እንዲህ ይላል፡- ‹የባሪያዬን ሶላት አሟልቶት ወይም አጉድሎ ሰግዶ እንደሆነ እዩለት› ይላል፡፡ የተሟላ ከሆነ (ምንዳው) የተሟላ ሆኖ ይጻፍለታል፡፡ የጎደለ ነገር ካለ ደግሞ ባሪያዬ የተጠው’ዉዕ ሶላት እንዳለው እዩለትና ተጠው’ዉዕ ካለው ‹‹ለባሪያዬ የግዴታ ሶላቱን ከተጠው’ዉዐ አሟሉለት› ይላል፡፡ የተቀሩት ሥራዎችም በዚሁ ዓይነት ይወሰዳሉ፡፡››[2]

## የተጠው’ዉዕ ሶላትን እቤት መስገድ ተመራጭ ነው

የጀማዓ ሶላት የተደነገገለት እንደ ተራዊሕ ያለው ሲቀር፣የተጠው’ዉዕ ሶላትን ከመስጊድ ይልቅ እቤት መስገድ ብልጫ አለው፡፡ ነቢዩ ﷺ ፡- ‹‹ከግዴታ ሶላት በስተቀር ያንድ ሰው በላጩ ሶላት እቤቱ የሚሰግደው ነው፡፡››[3] ብለዋል፡፡

(1) በቡኻሪ የተዘገበ
(2) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(3) በቡኻሪ የተዘገበ

### ማውጫ

የተጠው’ዉዕ ሶላት ትርጓሜ
የተጠው’ዉዕ ሶላት ትሩፋት
የተጠው’ዉዕ ሶላት ዓይነቶች
አንደኛ- የግዴታ ሶላት ተከታይ ሱንናዎች (ረዋቲብ)
ሁለተኛ- የውትር ሶላት
ሦስተኛ- የተራዊሕ ሶላት
አራተኛ- የዱሓ ሶላት
አምስተኛ- የመስጊድ መግቢያ ሶላት (ተሕይ’የቱል መስጅድ)
ስድስተኛ- የእስትኻራ ሶላት
ሰባተኛ- ከዉዱእ በኋላ ሁለት ረክዓ ሶላት
ስምንተኛ- ያልተገደበ (ሙጥለቅ) ተጠው’ዉዕ
ተጠው’ዉዕ የማይሰገድባቸው የተከለከሉ ወቅቶች



https://www.al-feqh.com/am

https://www.al-feqh.com/am







https://www.al-feqh.com/am

# የተጠው'ዉዕ ሶላት ዓይነቶች

የተጠው'ዉዕ ሶላት ብዙ ዓይነቶች ያሉት ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡-

## አንደኛ- የግዴታ ሶላት ቀዳሚና ተከታይ ሱንናዎች (ረዋትብ)[1]

የፈርድ ሶላቶችን የሚከተሉ ረዋትብ ሲሆኑ የጸኑ ሱንናዎች ናቸው።

የረዋትብ ሱንና በአጠቃላይ አስር ወይም አስራ ሁለት ረክዓዎች ናቸው። እነሱም ፡-

- ከፈጅር ሶላት በፊት ሁለት ረክዓ፤
- ሁለት ወይም አራት ረክዓ ከዙህር በፊትና ሁለት ረክዓ ከዙህር በኋላ፤
- ሁለት ረክዓ ከመግሪብ በኋላ፤
- ሁለት ረክዓ ከዕሻእ በኋላ ናቸው። እብን ዑመር ባስተላለፉት መሰረት፡- ‹‹ከነቢዩ ﷺ የያዝኩት አስር ረክዓዎችን ነው። ሁለት ረክዓ ከዙህር በፊት፣ሁለት ረክዓ ከዙህር በኋላ፣ሁለት ረክዓ ከመግሪብ በኋላ በቤታቸው፣ሁለት ረክዓ ከዕሻእ በኋላ በቤታቸውና ከሱብሕ ሶላት በፊት ሁለት ረክዓ ናቸው።››[2] ብለዋል። ከዙህር በፊት አራት ረክዓ ከማለታቸው ውጭ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ዘገባ ከዓእሻ (ረዐ) ተላልፏል።[3]

| ቀዳማይ ሱንና | የፈርድ ሶላት | ደህራይ ሱንና |
|---|---|---|
| ሁለት ረክዓ | የሱብሕ ሶላት | ------- |
| አራት ረክዓ | የዙህር ሶላት | ሁለት ረክዓ |
| ------- | የዐስር ሶላት | ------- |
| ------- | የመግሪብ ሶላት | ሁለት ረክዓ |
| ------- | የዕሻእ ሶላት | ሁለት ረክዓ |

(1) ረዋቲብ (ነጠላው ራቲብ) ቋሚና የጸና ነገር ማለት ነው።
(2) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(3) በሙስሊም የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am



ከረዋትብ ሱንናዎች ሁሉ በላጩና ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ከጉዞ ውጭና ተጓዥም ሆነው አዘውትረው የሰገዱት ሁለቱ የሱብሕ ቀዳሚ ሱንና ሶላት ነው፡፡ ዓኢሻ (ረዐ) ባስተላለፉት መሰረት ፡- ‹‹ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ከነዋፍል ውስጥ ከሁለቱ የፈጅር ረክዓዎች ይበልጥ አጥብቀው ይፈጽሙት የነበረ ሌላ ምንም አልነበረም፡፡››[1] ብለዋል፡፡

ዋጅቦቹን ካለማጓደል ጋር ረክዓዎቹን ቀለል አድርጎ መስገድ ሱንና ነው፡፡

ዓኢሻ (ረዐ) ባስተላለፉት መሰረት፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم ሁለቱን የፈጅር ሱንና ረክዓዎች ከሱብሕ ሶላት በፊት ሰገዱና ፋቲሓን ቀርተውበታል ወይ? ብዬ እስከምጠራጠር ድረስ ያሳጥሩ ነበር፡፡››[2] ብለዋል፡፡

የፈጅርን ሱንና ካመለጠ ሰግዶ መተካት የተፈቀደ ነው፡፡

1. ከሱብሕ ሶላት በኋላ፤ቀይስ ብን ዐምር ባስተላለፉት መሰረት የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم ከሱብሕ ሶላት በኋላ የሚሰግድ ሰው አይተው፡- ‹‹የሱብሕ ሶላት ሁለት ረክዓ ነው››[3]ሲሉት ፡- ‹‹ከበፊቱ ያለውን ሁለት ረክዓ አልሰገድኩምና ነው አሁን የሰገድኳቸው›› አላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم በዝምታ አለፉት ብለዋል፡፡

2. ጸሐይ ከወጣች በኋላ፤ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ፡- ‹‹የፈጅርን ሁለት ረክዓዎች ያልሰገደ ሰው ጸሐይ ከወጣች በኋላ ይስገዳቸው፡፡››[4] ብለዋልና፡፡



(1) [illegible]
(2) በቡኻሪና የተዘገበ
(3) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(4) በትርምዚ የተዘገበ

## ጠቃሚ ነጥቦች

- ከዙህር በፊት አራት ረክዓ መስገድ ያለው ትሩፋት በሐዲስ ተረጋግጧል፡፡ ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ፡- ‹‹ከዙህር በፊት አራት፣ከዙህር በኋላም አራት የሰገደን ሰው አላህ (ገላውን) በእሳት ላይ እርም አድርጓል፡፡››[1] ብለዋል፡፡

- ሙአክ'ከድ (የጸኑ) ካልሆኑ የተወደዱ (ሙስተሐብ) ሱንናዎች መካከል ከዐስር በፊት አራት ረክዓዎችን መስገድ አንዱ ነው፡፡ ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ፡- ‹‹ከዙህር በፊት አራት፣ከዙህር በኋላም አራት የሰገደን ሰው አላህ (ገላውን) በእሳት ላይ እርም አድርጓል፡፡››[2] ብለዋልና፡፡

- ከዐስር፣ከመግሪብና ከዕሻእ ሶላት በፊት ሱንናነቱ ያልጸና ሶላት መስገድ ተንግጓል፡፡ ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ፡- ‹‹በየሁለቱ አዛኖች መካከል ሶላት አለ - ሦስት ጊዜ ደጋግመው በሦስተኛው ላይ - ለፈለገ ሰው፡፡››[3] ብለዋል፡፡ ሁለት አዛኖች ማለት በየአዛኑና እቃማ መካከል ማለት ነው፡፡

- አንድ ሰው በእንቅልፍ ወይም በመርሳት ምክንት ያመለጠውን ሶላት፣መስገድ በተጠላበት ወቅትም ቢሆን ሰግዶ መተካት የተፈቀደ ነው፡፡ ነቢዩ صلى الله عليه وسلم የዙህርን ደህራይ ሱንና ሳይሰግዱ ቀርተው ከዐስር ሶላት በኋላ መስገዳቸው ተረጋግጧል፡፡

(1) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(2) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(3) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ



https://www.al-feqh.com/am

https://www.al-feqh.com/am



https://www.al-feqh.com/am

# ሁለተኛ- የውትር ሶላት

## የውትር ድንጋጌና ትሩፋቱ

ውትር የጠበቀ ጽኑ ሱንና ነው። ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹አላህ ውትር (አንድ) ነው፤ውትርን (ኢተጋማሽን) ይወዳልና የቁርኣን ባለቤቶች ሆይ! ውትርን ስገዱ፡ ፡››(1) ብለዋል። ነቢዩ ﷺ በሐዷርም ሆነ በሰፈር (እቤት እያሉም ሆነ በመንገደኝነት ጉዞ ላይ እያሉ) የውትር ሶላትን ተጠባብቀው ይሰግዱ ነበር።

## የውትር ሶላት አሰጋገድ

1. የውትር ሶላት አነስተኛ ረክዓ አንድ ሲሆን ከፍተኛው ቁጥር አስራ አንድ ወይም አስራ ሦስት ረክዓ ነው። የሚሰገደው በሁለት-ሁለት ረክዓ ሆኖ በማጠቃለያው አንድ ረክዓ ብቻ ይሰገዳል።

2. ዝቅተኛው የምሉእነት ቁጥሩ ሦስት ረክዓ ሲሆን፣ሁለት ረክዓ ተሰግዶ በሰላምታ ካበቃ በኋላ አንድ ነጠላ ረክዓ ይሰገዳል። ሦስቱንም አገናኝቶ በአንድ ተሸሁድ ብቻ መስገድም ይቻላል። በመጀመሪያው ረክዓ ከፋቲሓ በኋላ ሱረቱል አዕላን፣ በሁለተኛው ሱረቱል ካፍሩንን፣በሦስተኛው ሱረቱል እኽላስን መቅራት ሱንና ነው። ኡበይይ ብን ከዕብ ባስተላለፉት መሰረት ፦ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ﷺ በውትር የመጀመሪያው ረክዓ ‹ሰብ'ብሕ እስመ ረብብከል አዕላ›፤በሁለተኛው ‹ቁል ያ አዩ'ዩሀል ካፍሩን››፤በሦስተኛው ‹ቁል ሁወል'ሏ.ሁ አሐድ› ይቀሩ ነበር።››(2) ብለዋል።

## የውትር ሶላት ወቅት

ከዕሻእ ሶላት በኋላ እስከ ጎሕ መቅደድ ድረስ ነው። በሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ መስገዱ በላጭ ነው። ከጃቢር በተላለፈው ሐዲስ ነቢዩ ﷺ ‹‹በሌሊቱ መጨረሻ ላይ አልነቃም ብሎ የፈራ ሰው ውትርን በሌሊቱ መጀመሪያ ላይ ይስገድ።››(3) ብለዋል። ነቢዩ ﷺ ‹‹በአንድ ሌሊት ሁለት ውትር የለም››(4) በማለታቸው ውትር ሁለት ጊዜ አይሰገድም። በተጨማሪም ነቢዩ ﷺ ፦ ‹‹በ(ሌሊቱ) መጨረሻ ለመነሳት ተስፋ ያደረገ ሰው ውትሩን በሌሊቱ መጨረሻ ይስገድ፤በሌሊቱ መጨረሻ የሚሰገድ ሶላት መላእኮች የሚጣዱት ነውና በላጭ ነው።››(5) ብለዋል።

(1) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(2) በነሳኢ የተዘገበ
(3) በሙስሊም የተዘገበ
(4) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(5) በሙስሊም የተዘገበ

## የውትር ዱዓእ (ቁኑት)

በውትር ሶላት የመጨረሻው ረክዓ ከሩከዕ በፊት ወይም ከሩኩዕ ቀና ካሉ በኋላ ዱዓእ ማድረግ የተደነገገ ነው። በዱዓኡ ላይ ሁለት እጆችን ከፍ አድርጎ ከተላለፉት የዱዓእ ዓይነቶች አንዱን ያደርጋል። ከነዚህም የሚከተለውን እናገኛለን፦ ‹‹አል'ሏሁም'መ እህድኒ ፊመን ሀደይተ፣ወዓፍኒ ፊመን ዓፈይተ፣ወተወል'ለኒ ፊመን ተወል'ለይተ፣ወባሪክሊ ፊማ አዕጠይተ፣ወቅኒ ሸር'ረ ማቀዷይተ፣ፈእን'ነከ ተቅዷ ወላዩቅዷ ዐለይከ፣እን'ነሁ ላየዝልሉ መን ዋለይተ፣ወላየዕዝ'ዙ መን ዓደይተ፣ተባረክተ ረብ'በና ወተዓለይተ›› ትርጉሙ ፦ ‹‹አላህ ሆይ! ከተመሩት ጋር ወደ ቀጥተኛው መንገድ ምራኝ። ከዳኑትም ጋር አድነኝ፡ ከተወዳጀሃቸው ጋርም ተወዳጀኝ። የሰጠኸኝን ባርክልኝ። ከወሰንከው ክፉ ነገርም ጠብቀኝ። አንተ ወሳኝና ፈራጅ ስትኾን ባንተ ላይ የሚወስን የለምና፡ አንተ ያገዝኸው አይዋረድም፤አንተ የጠላኸውም አያሸንፍም። ጌታችን ሆይ! አንተ የቅድስናና የልቅና ባለቤት ነህና።››

- ኢማሙ ቁኑት (ዱዓእ) ሲያደርግ ከኋላው ያሉት፣የአላህ ውዳሴን በተመለከተው ሳይሆን በልመናው ክፍል ብቻ ኣሚን ይላሉ። ለምሳሌ ‹‹ፈእን'ነከ ተቅዷ ወላዩቅዷ ዐለይከ›› የሚለውን በመሳሰለ ውዳሴ ኣሚን አይባልም።

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ከውትር ሶላት በኋላ ሦስት ጊዜ ‹‹ሱብሓነል መሊክል ቁድ'ዱስ›› ማለት ሱንና ነው፡ ፡ በሦስተኛው ላይ ጎተት አርጎ ድምጹን ከፍ ያደርጋል። ‹‹ረብ'ቡል መላእከት ወር'ሩሕ›› የሚለውን መጨመርም ይችላል፡

2. ከነቢዩ ﷺ ያልተላለፈ በመሆኑ ከውትር ዱዓእም ሆነ ከማንኛውም ዱዓእ በኋላ ፊትን ማበስ የተደነገገ አይደለም።

3. ቁኑት ዓመቱን በሙሉ የተፈቀደ ሲሆን ለረመዳን ሁለተኛ አጋማሽ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ደራሽ አደጋ በሚኖርበት ጊዜ በሁሉም የግዴታ ሶላቶች ቁኑት ማድረግ ሙስተሐብ ነው።

4. የቁርኣን ኸትም ዱዓን ሶላት ውስጥ ማድረግ አልተደነገገም።

https://www.al-feqh.com/am

## ውትርን ቀን ሰግዶ መተካት

ውትርን ቀን ሰግዶ መክፈል የተደነገገ ሲሆን ሁለት ሁለት በመስገድ ይካካሳል፡ ከዓእሻ በተላለፈው መሰረት ‹‹የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት የሌሊት ሶላት ሲያመልጣቸው በቀን አስራ ሁለት ረክዓ ይሰግዱ ነበር፡፡ ››[1]ብለዋል፡፡

(1) በሙስሊም የተዘገበ

## የተራዊሕ ሶላትን በዕሻእ ንይ’ያ

ከዕሻእ ሶላት ዘግይቶ ሰዎች ተራዊሕ ሲሰግዱ የደረሰ ሰው በዕሻእ ንይ’ያ ከነሱ ጋር ወደ ሶላቱ ይገባል፡፡ ኢማሙ ሰላምታ ሲል ተነስቶ ያሚለዋል፡፡

## ሦስተኛ- የተራዊሕ ሶላት

ተራዊሕ፡ በረመዷን የሚሰገድ የሌሊት ሶላት ነው፡፡ ተራዊሕ (መታረፊያ) የተባለው ሶላቱ በመርዘሙ ምክንያት በየአራት ረክዓው ጣልቃ ያርፉበት ስለነበረ ነው፡፡

### የተራዊሕ ሶላት ትሩፋት

በተባረከው የረመዷን ወር የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم ለቀናት ከሰሓቦች ጋር ሰግደው ከዚያ በኋላ ግዴታ ሆኖ እንዳይደነገግ በመፍራት የተውት የጸና ሱንና ነው፡፡ ከሳቸው በኋላም ሶሓባቸው رضي الله عنه ሰግደውታል፡፡[1]

### የተራዊሕ ሶላት ረክዓ ብዛት

በላጩ አስራ አንድ ረክዓ ነው፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ صلى الله عليه وسلم በብዛት በተግባር የፈጸሙት ይህ በመሆኑ ነው፡፡ እመ ምእመናን ዓእሻ (ረዐ) በረመዳን የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم ሶላት እንዴት እንደነበረ ተጠይቀው ‹‹የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم በረመዳንም ሆነ በሌላ ጊዜ ከአስራ አንድ ረክዓ አይጨምሩም ነበር፡፡››[2] ብለዋል፡፡

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(2) በሙስሊም የተዘገበ



ለሶላት ከእንቅልፍ መንቃት

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የሌሊት ሶላት (ቅያሙል’ለይል) ዓመቱን በሙሉ የጠበቀ ሱንና ነው፡፡ የሌሊት ሶላትን መተው የተጠላ (መክሩህ) ነው፡፡ ዐብዱላህ ብን መስዑድ (ረዐ) ባስተላለፉት መሰረት አንድ ሰውዬ ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ዘንድ ተወሳና ‹‹እስኪነጋ ድረስ አሁንም እየተኛ ነው፣ለሌሊት ሶላትም አልተነሳም›› ሲበል፣ነቢዩ صلى الله عليه وسلم :- ‹‹ሰይጣን በጆሮው ሸንቶበታል፡፡››[1] አሉ፡ አንድ ሰው ያስለመደውን የሌሊት ሶላት መተው የተጠላ ነው፡፡ ከዐብዱላህ ብን ዐምር ብን አልዓስ (ረዐ) በተላለፈው መሰረት የአላህ መልእክተኛ صلى الله عليه وسلم :- ‹‹ዐብደላህ ሆይ! ሌሊት ለሶላት ይነሳ እንደነበረውና ኋላ የሌሊት ሶላቱን እንደ ተወው እገሌ ዓይነት አትሆን፡፡›› አሉኝ ብለዋል፡፡
2. ማታ ሲተኙ ተነስቶ ለመስገድ ንይ’ያ አድርጎ መተኛት የተወደደ ነው፡፡ ከእንቅልፉ የነቃ ሰው ይህን አስመልክቶ በተላለፉት አዝካር አላህን መዘከር፣እንቅልፉን ከፊቱ ማበስና ጥርሱን

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am



መፋቅ ሱንና ነው። ሑዘይፋ (ረዐ) ባስተላለፉት መሰረት ‹‹የአላህ መልእክተኛ ሌሊት ሲነሱ ﷺ አፋቸውን በመፋቂያ ያጸዱ (ጥርሳቸውን ይፋቁ)[1]፣ወደ ሰማይ ይመለከቱ፣ከኣሊ ዒምራን ምዕራፍ የመጨረሻዎቹን አስር አንቀጾችም ይቀሩ ነበር።›› ብለዋል።

ከእብን ዐባስ (ረዐ) በተላለፈው መሰረት እመ ምእመናን መይሙና (ረዐ) ቤት - የሹሜያቸው ናቸው - አድሬ በአንድ ሰሌን አግድሙ ላይ ተኛሁ፤የአላህ መልእክተኛና ባለ ቤታቸው በሰሌኑ ቁመት ተኙ። እስከ ሌሊቱ አጋማሽ ወይም ወደዚያው አካባቢ ድረስ ተኙና ከእንቅልፍ ነቅተው እንቅልፉን ከፊታቸው አባበሱ። በሌላ ዘገባ ተነስተው ተቀመጡና ወደ ሰማይ ተመልክተው ከኣሊ ዒምራን ምዕራፍ አስር አንቀጾችን ቀሩ። በሌላ ተጨማሪ ዘገባ ደግሞ ከኣሊ ዒምራን ምዕራፍ የመጨረሻዎቹን አስር አንቀጾችን ቀሩ የሚል ተመልክቷል።

አንድ ሰው ለሌሊት ሶላት ሲነሳ ሚስቱን ለሶለቱ መቀስቀስ፣ሚስቲቱም እንደዚሁ ከተነሳች ባሏን መቀስቀስ የተወደደ ነው። ነቢዩ ﷺ :- ‹‹አንድ ሰው ሌሊት ባለቤቱን ቀስቅሶ አንድ ላይ ሁለት ረክዓ ከሰገዱ አላህን ከሚያወሱ ወንዶችና ሴቶች ጋር ይመዘገባሉ።››[2]ብለዋል።

3. የሌሊት ሶላት እየሰገደ እንቅልፍ ያሸነፈው ሰው ሶለቱን ይተውና እንቅልፉ እስኪሄድለት ይተኛል፡ ከዓእሻ (ረዐ) በተላለፈው መሰረት ነቢዩ ﷺ ‹‹አንዳችሁ ሶላት ውስጥ እንቅልፍ ከተጫጫነው እንቅልፉ እስኪለቀው ድረስ ይተኛ፤አንዳችሁ እያንቀላፋ ከሰገደ ምናልባት እስትግፋር አደርጋለሁ ብሎ ራሱን ሊሰድብ (ሊረግም) ይችላልና።››[3]ብለዋል። በሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ እስትግፋርና ዱዓእ ማድረግ የተወደደ ነው፡ ፡ ከአቡ ሁረይራ (ረዐ) በተላለፈው መሰረት የአላህ መልእክተኛ ﷺ :- ‹‹አላህ ﷻ በሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ ወደ ቅርቢቱ ሰማይ ይወርድና :- ማነው የሚለምነኝና የምሰማለት? ማነው የሚጠይቀኝና የምሰጠው? ማነው ምሕረት የሚለምነኝና ምሕረት የማደርግለት? ይላል። ››[4]ብለዋል።

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(2) በአቡ ዳዉድ የተዘገበ
(3) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ
(4) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ

# አራተኛ- የዱሓ ሶላት

በዱሓ ጊዜ (ረፋድ ላይ) የሚሰገድ ሶላት ነው። የዱሓ ወቅት ጸሐይ ወጥታ በዓይን ግምት የጦር ዘንግ ያህል ከፍ ካለችበት - ከፍታው የሃያ ደቂቃ ያህል ቆይታ ነው - ጊዜ ጀምሮ ጸሐይ ከአናት አለፍ ከማለቷ ከአስራ አምስት ወይም ከሃያ ደቂቃ በፊት ያለው ጊዜ ነው። በላጬ የመሰገጃ ጊዜ ሙቀቱ መበርታት በሚጀምርበት ጊዜ ነው። ነቢዩ ﷺ :- ‹‹የወደ አላህ ተመላሾች ሶላት (ሶላቱል አውዋቢን) የግመል ጥጃዎች ኮቴ በአሸዋው ሙቀት በሚለበለብበት ጊዜ ነው።››[5] ብለዋልና፡

## የዱሓ ሶላት ትሩፋት

አላህ ﷻ ሐዲስ አልቁድሲ ውስጥ :- ‹‹የኣደም ልጅ ሆይ! በቀኑ መጀመሪያ ላይ አራት ረክዓዎችን ለኔ ስገድና (ለጉዳዩችህ እስከ ቀኑ) መጨረሻ እኔ እበቀሃለሁ።›› ብሏል።

## የዱሓ ሶላት ረክዓ ቁጥር

ሁለት፣ወይም አራት፣ወይም ስድስት፣ወይም ስምንት ረክዓ መስገድ ይቻላል፡ ትክክለኛው እያንዳንዱን ሁለት ረክዓ በሰላምታ በማብቃት መስገድ ነው። ከነቢዩ ﷺ በተግባር የተረጋገጠው በሁለት ሁለት ረክዓ መስገድ ነውና።

- የዱሓ ሶላት በያንዳንዱ የሰው አካል መገጣጠሚያ አጥንት ቁጥር ምጽዋት መስጠትን ያህል አጅር የሚያስገኝ ነው። ነቢዩ ﷺ :- ‹‹በያንዳንዳችሁ መገጣጠሚያና አጥንት ላይ የሚሰጥ ምጽዋት (ሶደቃ) አለ። እያንዳንዱ ተስቢሕ (ሱብሓነል'ኋህ ማለት) ምጽዋት ነው። እያንዳንዱ ተሕሚድ (አልሐምዱሊል'ላህ ማለት) ምጽዋት ነው። እያንዳንዱ ተሕሊል (ላእላሀ እል'ላል'ኋህ ማለት) ምጽዋት ነው። እያንዳንዱ ተክቢራ (አል'ኋሁ አክበር ማለት) ምጽዋት ነው። ወደ በጎ ነገር ማዘዝ ምጽዋት ነው። ከእኩይ ነገር መከልከልም ምጽዋት ነው። ከዱሓ (ሶላት) የሚሰግደው ሁለት ረክዓም ይህንኑ ይሸፍናል።››[6] ብለዋል።

- አራት ረክዓ ዱሓ የሰገደ ሰው እለቱን አላህ በቂው ነው። ከኑዐይም ብን ሀማር አልገጥፋኒ በተላለፈውና የአላህ መልእክተኛ ከጌታቸው ﷻ በሚተላለፍላቸው ሐዲስ አልቁድሲ ውስጥ :- ‹‹የኣደም ልጅ ሆይ!

(5) በሙስሊም የተዘገበ
(6) በሙስሊም የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am

በቀኑ መጀመሪያ ላይ አራት ረክዓዎችን ለኔ ስገድና (ለጉዳዩችህ እስከ ቀኑ) መጨረሻ እኔ እበቀዛለሁ:: ››[1] ብሏል::

- የሱብሕ ሶላትን በጀማዓ ሰግዶ ጸሐይ እስክትወጣ ድረስ አላህን በመዘከር ከቆየ በኋላ ዱሓን የሰገደው ሰው የተሟላ ሐጅና ዑምራ አጅር ያገኛል: የአላህ መልእክተኛ ﷺ :- ‹‹የንጋት ሶላትን በጀማዓ የሰገደ፣ከዚያም ጸሐይ እሰክትወጣ ድረስ ቁጭ ብሎ አላህን የዘከረ፣ከዚያ ሁለት ረክዓ የሰገደ ሰው የአንድ ሐጅና ዑምራ ያህል ምንዳ ያገኛል::›› ብለዋል:: የአላህ መልእክተኛ ﷺ :- ‹‹የተሟላ፣የተሟላ፣የተሟላ (አጅር)››[2]ብለዋል::



(1) በሙስሊም የተዘገበ
(2) በትርምዚ የተዘገበ ሲሆን አልባኒ ሶሒሕ ነው ብለውታል

## የዱሓ ሶላት ረክዓ ቁጥር

ሁለት፣ወይም አራት፣ወይም ስድስት፣ወይም ስምንት ረክዓ መስገድ ይቻላል: ትክክለኛው እያንዳንዱን ሁለት ረክዓ በሰላምታ በማብቃት መስገድ ነው:: ከነቢዩ ﷺ በተግባር የተረጋገጠው በሁለት ሁለት ረክዓ መስገድ ነውና::

- የዱሓ ሶላት በያንዳንዱ የሰው አካል መገጣጠሚያ አጥንት ቁጥር ምጽዋት መስጠትን ያህል አጅር የሚያስገኝ ነው:: ነቢዩ ﷺ :- ‹‹በያንዳንዳችሁ መገጣጠሚያና አጥንት ላይ የሚሰጥ ምጽዋት (ሶደቃ) አለ:: እያንዳንዱ ተስቢሕ (ሱብሓነል'ላህ ማለት) ምጽዋት ነው:: እያንዳንዱ ተሕሚድ (አልሐምዱሊል'ላህ ማለት) ምጽዋት ነው:: እያንዳንዱ ተሕሊል (ላእላሀ እል'ላል'ሏህ ማለት) ምጽዋት ነው:: እያንዳንዱ ተክቢራ (አል'ሏሁ አክበር ማለት) ምጽዋት ነው:: ወደ በጎ ነገር ማዘዝ ምጽዋት ነው:: ከእኩይ ነገር መከልከልም ምጽዋት ነው:: ከዱሓ (ሶላት) የሚሰግደው ሁለት ረክዓም ይህንኑ ይሸፍናል::››[3] ብለዋል::

- አራት ረክዓ ዱሓ የሰገደ ሰው እለቱን አላህ በቂው ነው:: ከኑዐይም ብን ሀማር አልገጥፋኒ በተላለፈውና የአላህ መልእክተኛ ከጌታቸው ﷻ በሚተላለፍላቸው ሐዲስ አልቁድሲ ውስጥ :- ‹‹የኣደም ልጅ ሆይ! በቀኑ መጀመሪያ ላይ አራት ረክዓዎችን ለኔ ስገድና (ለጉዳዩችህ እስከ ቀኑ) መጨረሻ እኔ እበቀዛለሁ:: ››[4] ብሏል::

- የሱብሕ ሶላትን በጀማዓ ሰግዶ ጸሐይ እስክትወጣ ድረስ አላህን በመዘከር ከቆየ በኋላ ዱሓን የሰገደው ሰው የተሟላ ሐጅና ዑምራ አጅር ያገኛል: የአላህ መልእክተኛ ﷺ :- ‹‹የንጋት ሶላትን በጀማዓ የሰገደ፣ከዚያም ጸሐይ እሰክትወጣ ድረስ ቁጭ ብሎ አላህን የዘከረ፣ከዚያ ሁለት ረክዓ የሰገደ ሰው የአንድ ሐጅና ዑምራ ያህል ምንዳ ያገኛል::›› ብለዋል:: የአላህ መልእክተኛ ﷺ :- ‹‹የተሟላ፣የተሟላ፣የተሟላ (አጅር)››[5]ብለዋል::

(3) በሙስሊም የተዘገበ
(4) በሙስሊም የተዘገበ
(5) በትርምዚ የተዘገበ ሲሆን አልባኒ ሶሒሕ ነው ብለውታል

https://www.al-feqh.com/am



## አምስተኛ - የመስጊድ መግቢያ ሶላት (ተሕይ'የቱል መስጅድ)

መስጊድ የገባ ሰው ከመቀመጡ በፊት እንዲሰግዳቸው የተደነገገ ሁለት ረክዓ ሶላት ነው፡ ብያኔው የጸና ሱንና ነው። ማስረጃው ነቢዩ ﷺ ፡- ‹‹አንዳችሁ መስጊድ ከገባ ከመቀመጡ በፊት ሁለት ረክዓዎችን ይስገድ።››[1] ማለታቸው ነው።

ራትብ የሆነ ሱንና ወይም የግዴታ ሶላትም ሊተካው ይችላል። ለምሳሌ ዙህር ለመስገድ መስጊድ የገባ ሰው ከመቀመጡ በፊት የዙህርን ሱንና ከሰገደ የተሕይ'የቱል መስጅድ ሶላትን መተካት ይችላል።



ተሕይ'የቱል መስጅድ

## ስድስተኛ - የእስትኻራ ሶላት

አንድ ሰው በአንድ ጉዳይ ላይ ግራ ተጋብቶ መወሰን ሲያቅተው ከመቁረጡ በፊት የሚሰግደው ሁለት ረክዓ ሶላት ነው። ለተሻለው ነገር ለመመራት አንድ የአላህ አገልጋይ ማድረግና አለማድረግ በሚችልባቸው ነገሮች ላይ የሚበጀውን ለመምረጥ የተደነገገ ሶላት ነው። ከሶላቱ በኋላ ዱዓእ ያደርጋል፡ ፡ ነቢዩ ﷺ የቁርኣን ምዕራፍን ያስተምሯቸው እንደነበረ ሁሉ ለሶሓባ እስትኻራንም ያስምሯቸው ነበር።

### የእስትኻራ ዱዓእ

ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ‹‹አንዳችሁ የሆነ ጉዳይ ካሰበ የግዴታ ያልሆነ ሁለት ረክዓ ይስገድና ‹አል'ሏሁምመ እን'ኒ አስተኺሩከ ብዕልምከ፣ወአስተቅድሩከ ብቁድረትከ፣ወአስአሉከ ምን ፈድሊከል ዐዚም፣ፈእን'ነከ ተቅድሩ ወላ አቅድሩ፣ወተዕለሙ ወላአዕለሙ፣ወአንተ ዐልላሙልጉዩብ። አል'ሏሁም'መ ﷻ' እንኩንተ ተዕለሙ አን'ነ ሃዘል አምር ኸይሩን ሊፊዲኒ ወመዓሺ ወዓቅበት አምሪ - አው ዓጅሊሂ ወኣጅሊሀ ፣ፈቅድርሁ ሊ ወየስሲርሁ ሊ ሡም'መ ባሪክ ሊ ፊህ፣ወእን ኩንተ ተዕለሙ አን'ነ ሃዘል አምር ሸርሩን ሊ ፊዲኒ ወመዓሺ ወዓቅበት አምሪ - አው ዓጅል አምሪ ወኣጅሊሀ -፣ፈስሪፍሁ ዐን'ኒ ወስሪፍኒ ዐንሁ፣ወቅዱር ሊየል ኸይረ ሐይሡ ካነ፣ሡም'መ አርድኒ ብህ፣ይበል።›› ብለዋል።

ትርጉሙ፡- ‹‹አላህ ሆይ! በእውቀትህ መልካሙን ነገር እንድትመርጥልኝ እለምነሃለሁ፣የሚበጀኝን በኃይልህ እንድት ወስንልኝ እለምንሃለሁ። ከታላቁ ችሮታህ እንድትለግሰኝም እጠይቀሃለሁ። አንተ ሁሉን ቻይ ስትሆን እኔ አቅመ ቢስ ደካማ ነኝና፡ እኔ ምንም የማላውቅ ስሆን አንተ ከሕዋስ ስሜት የራቀውን ሁሉ ፍጹም ዐዋቂ ነህና። አላህ ሆይ! ይህ ጉዳይ (ጉዳዩን ይጠቅስና) ለሃይማኖቴና ለዓለማዊ ሕይወቴ፣ለመጨረሻዩም የማይበጅ ከሆነ ከኔ አስወግድልኝና እኔንም ከርሱ መልሰኝ፡ የሚሻለኝን ነገር ባለበት ወስንልኝና (ነገሩን) አስወድደኝ። ››[2]ማለት ነው።

> **የእስትኻራ ምልክት**
>
> እስትኻራን ደጋግሞ መስገድ ችግር የለውም። እስትኻራ ያደረገ ሰው ጉዳዩን የሚገልጽለት ሕልም ማየት ሸርጥ አይደለም። ማድረግ ያለበት፣ኃጢአት ወይም ዝምድናን መቁረጥ እስከሌለበት ድረስ አላህን ለምኖ በመረጠው ነገር ወደፊት መቀጠል ብቻ ነው። ከተሳካ መልካም፣ካልተሳካም መልካሙ እሱ ነው።

(1) በቡኻሪና ሙስሊም የተዘገበ

(2) በቡኻሪ የተዘገበ

https://www.al-feqh.com/am

## ሰባተኛ - ሁለት ረክዓ ከዉዱእ በኋላ

አቡ ሁረይራ (ረዐ) ባስተላለፉት መሰረት ነቢዩ صلى الله عليه وسلم በፈጅር ሶላት ጊዜ ለቢላል (ረዐ) ፡- ‹‹ቢላል ሆይ! በጀነት ውስጥ የጫማዎችህን ኮሽታ ከፊት ለፊቴ ሰምቻለሁና በእስላም ውስጥ የሰራኸውን ከሁሉም በላይ ተስፋ የምታደርግበትን ሥራ ንገረኝ፡፡›› ሲሏቸው ቢላል፡- ‹‹በሌሊትም ሆነ በቀን ሰዓት በዚያ ዉዱእ የተጻፈልኝን ያህል ሶላት የምሰግድ ብሆን እንጅ ዉዱእ አድርጌ የማላውቅ ከመሆን ውጭ እኔ ዘንድ ተስፋ የሚጣልበት ሥራ አልሰራሁም፡፡›› [1] ብለዋል፡፡


## ስምንተኛ - ያልተገደበ (ሙጥለቅ) ተጠውዉዕ

ሙጥለቅ ተጠው'ዉዕ በጊዜም ሆነ በምክንያት ያልተገደበ ሶላት ነው፡፡ ያልተገደበ ተጠው'ዉዕ መስገድ ከሚከለከልባቸው ወቅቶች ውጭ ሁሌ መስገዱ የተደነገገ ሶላት ነው፡፡

## ያልተገደበ (ሙጥለቅ ተጠው'ዉዕ ሶላት ምሣሌዎች

### የሌሊት ሶላት (ቅያሙል›ለይል)

ነቢዩ صلى الله عليه وسلم እንዲህ ፡- ‹‹ከግዴታ ሶላት በኋላ በላጩ ሶላት የሌሊት ሶላት ነው፡፡››[2] ብለዋል፡ በተጨማሪም ነቢዩ صلى الله عليه وسلم ፡- ‹‹ጀነት ውስጥ ውጭያቸው ከውስጥ፣ውስጣቸውም ከውጭያቸው የሚታዩ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡›› ሲሉ አንዱ ገጠሬ ዐረብ ተነሳና የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ለማን ናቸው? አላቸው፡፡ እሳቸውም ፡- ‹‹አንደበቱ ጥሩ ጥሩውን ለሚናገር፣ምግብ ለሚያበላ፣ጾምን ለሚያዘወትርና ሰዎች ሲተኙ ለአላህ ሌሊት ለሚሰግድ ሰው ናቸው፡፡››[3] አሉት፡፡



“

### የሌሊት ሶላት በሕክምና

ሌሊት ተነስቶ መስገድ፣በተለይም ከመንቃት በፊት ብዙ ሰዓታት ቀደም ቢሎ የሰውነታችን ተፈጥሯዊ የኮርቲዞልና የኮርቲዞን ሆርሞኖች እንዲቀንሱ ይረዳል፡ ወቅቱ ከመጨረሻው የሌሊት ሲሶ ጋር የሚገጣጠም ነው፡፡ ይህም በሱካር ሕሙማን ላይ አደጋ የሚጋርጠውን በደም ውስጥ ድንገተኛ የሆነ የስኳር መጠን ጭማሪ እንዳይከሰት ይከላከላል፡፡

”

(1) በቡኻሪ የተዘገበ
(2) በሙስሊም የተዘገበ
(3) በትርምዚ የተዘገበ


https://www.al-feqh.com/am



https://www.al-feqh.com/am

## ምክንያት ያላቸው ሶላቶች በተከለከሉ ወቅቶች

ምክንያት ያላቸው እንደ ተሕይ'የቱል መስጅድና እንደ ጀናዛ ያሉ ሶላቶችን፣መስገድ በተከለከለባቸው ጊዜያት እንኳ ቢሆን መስገድ ይፈቀዳል፡፡



## ሶላት መስገድ የተከለከለባቸው ወቅቶች

1. ከፈጅር ሶላት በኋላ ጸሐይ ወጥታ በዓይን ግምት የጦር ዘንግ ያህል ከፍ እስከምትል ድረስ፡፡ ይህ በተለምዶ የሃያ ደቂቃዎች ያህል ቆይታ ነው፡፡
2. ጸሐይ ልክ አናት ላይ ከሆነችበት ጊዜ ዘንበል እስክትል ድረስ፡፡
3. ከዐስር ሶላት በኋላ እስክትጠልቅ ድረስ፡፡

ማስረጃው ዑቅባ ብን ዓምር (ረዐ) ባስተላለፉት መሰረት ፡- ‹‹የአላህ መልእክተኛ ﷺ በሦስት ጊዜያት ውስጥ እንዳንሰግድባቸው፣ሙታንን እንዳንቀብርባቸው ይከለክሉን ነበር፡፡ እነሱም ፡- ጸሐይ ጎላ ብላ በምትወጣበት ጊዜ ከፍ እስክትል ድረስ፣ቀትር ላይ ጸሐይ ከአናት አለፍ እስክትል ድረስና ጸሐይ ለመጥለቅ ስትቃረብ እስክትጠልቅ ድረስ ናቸው፡፡››(1)



(1) በሙስሊም የተዘገበ